

ጥያቄዎች በ ወላጆች ለወላጆች

የትምህርት አመት 2027-28

MY SCHOOL DC
የሕዝብ ት/ቤት ሎተሪ
MySchoolDC.org

መግቢያ

በዲስትሪክቱ ውስጥ በርካታ የሕዝብ ትምህርት ቤት አማራጮች በመኖራቸው፣ ወላጆች እና አሳዳጊዎች የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለባቸው ልጆቻቸው የእኔ ትምህርት ቤት ብለው የሚጠሩትን ትምህርት ቤት ለማግኘት። ከMy School DC የወላጅ አማካሪ ምክር ቤት (PAC) የመጡ የወላጅ ተወካዮች እርስዎን ለማስጀመር እንዲረዱ እነዚህን የጥያቄዎች ዝርዝር አውጥቷል። መሰረታዊ መረጃ ለማግኘት በ **MySchoolDC.org** የትምህርት ቤት የኦነላይን ፕሮፋይልን ይጎብኙ፣ እና የትምህርት ቤት ሰራተኞን መጠየቅ የሚፈልጉ ጥያቄዎች አጠገብ ☑ የምርጫ ምልክት ያስቀምጡ። እነርሱን ወደ EdFEST፣ የትምህርት ቤት ዝግጅቶች እና የትምህርት ቤት መክፈቻ ቤቶች ጭምር ይዘዋቸው እንደሚሄዱ ያረጋግጡ!

የትምህርት ቤት ፖሊሲዎች እና የድጋፍ አገልግሎቶችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ የበፊት እና የኋላ እንክብካቤን ያቀርባሉ? ለበፊት እና ኋላ የእንክብካቤ ፕሮግራማችሁ እንዴት ማመልከት እችላለሁ? በእርሱ ፍላጎት ላላቸው ሁሉም ቤተሰቦች በቂ ክፍል አለ?
- ☐ የበፊት እና የኋላ የእንክብካቤ ፕሮግራሞቻችሁ በትምህርት ቤቱ ወይስ በውጭ ድርጅት ነው የምተዳደረው? ፕሮግራም አወጣጡ ከትምህርት ቤት የትምህርት ሥርዓት ጋር እንዴት ይሄዳል?
- ☐ የትምህርት ቤትዎ ደንብ ልብሶች ወይም የአለባበስ ኮዶች ምንድን ናቸው? በደንብ ልብሱ ወጪ ቤተሰቦችን ይረዳሉ?
- ☐ ትምህርት ቤትዎን እንደ አማራጭ ለመውሰድ ስናስብ ከግምት ማስገባት ያሉብን የትምህርት ቤትዎ ፕሮግራም ላይ የሚጨመሩ ወጪዎች አሉ?
- ☐ ልጄ የትርፍ ጊዜ ትምህርት ከፈለግ/ች፣ ይገኝላቸዋል? ተጨማሪ ድጋፎችን ለተማሪዎች ለማቅረብ ከውጪ ድርጅቶች ጋር አጋርነት ይፈጥራሉ (ለምሳሌ፣ ከፍተኛ ስኬት፣ የንባብ አጋሮች)?
- ☐ ምን ዓይነት ስፖርቶች፣ ክለቦች፣ እና ሌሎች ከትምህርት ጊዜ ውጪ ተግባራትን ያቀርባሉ? እነርሱ ለሁሉም ተማሪዎች ይገኛሉ፣ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎችን ጨምሮ? ተማሪዎች እንዲሳተፉባቸው ከእነዚህ ተግባራት ጋር የተያያዙ ወጪዎች አሉ? የተገደቡ ቦታዎች አሉ ወይም ክፍት ቦታ አለ?
- ☐ የበጋ ፕሮግራም አላችሁ? የሚኖራችሁ ከሆነ፣ ምን ወጪ ይጠይቃል? ቮቸሮች ተቀባይነት አላቸው? ለሁሉም ተማሪዎች ይኖራል?
- ☐ የባህሪ ቁጥጥር እና ሥነ-ምግባር ጋር በተያያዘ የትምህርት ቤትዎን ባህል እና ፖሊሲዎችን ግለጹ። ለምሳሌ፣ የተሃድሶ ፍትህ አካሄድ ትጠቀማላችሁ? የባህሪ መቆጣጠር ጉዳዮች የሚያጋጥሟቸው ተማሪዎችን ለማገዝ ምን ዓይነት የድጋፍ ሥራተኛ አለ?
- ☐ የክትትል ፖሊሲያችሁ ምንድን ነው?
- ☐ ተጨማሪ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች ጋር ወይም በአጠቃላይ ከቤተሰቦች ጋር የሚሰራ ቁርጠኛ የሆነ የወላጅ ግንኙነት ወይም የወላጅ ተሳትፎ ሠራተኛ ሰው አላችሁ?

የትምህርት ቤት ትምህርት ሥርዓት የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ የትምህርት ቤታችሁ የትምህርት ሞዴል ምንድን ነው (ለምሳሌ፣ የአዕምሮ መሳሪያዎች)? ወላጆች ልጆቻቸው ስለ ምን እየተማሩ እንደሆነ እንዴት ማወቅ ይችላሉ?
- ☐ የትምህርት ቤታችሁ የትምህርት ፍልስፍና ምንድን ነው እና በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ እንዴት ይገባል? ለምሳሌ፣ እንደ ወሳኝ ውድድር ንድፈ ሃሳብ ወይም ማህበራዊ ፍትህ ዓይነት ጽንሰ-ሀሳቦች በትምህርት ይሰጣሉ?
- ☐ በትምህርት ሥርዓታችሁ ውስጥ ለባህል ምላሽ የሚሰጡ አስተምሮን ታካትታላችሁ? ከሆነ፣ እንዴት አድርጋችሁ?
- ☐ እባክዎ የማህበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርት ላይ የትምህርት ቤታችሁን አቀራረብ ግለጹ።
- ☐ ተማሪዎችን የተለያዩ የስራ-መስኮች እና ቴክኒክ ትምህርት ጋር ለማስተዋወቅ ከውጪ ድርጅቶች ጋር አጋርነት ትፈጥራላችሁ?
- ☐ ለኮሌጅ እና ሥራ-መስኮች ዝግጁነት ግምገማ አጋርነት (PARCC) ፈተና የፈተና ዝግጅት ምን ይመስላል?
- ☐ በትምህርት ቤታችሁ የተለመደው የትምህርት ክፍል የጊዜ ሰሌዳ ምንድን ነው?
- ☐ ልጄ በየቀኑ ለመቀበል መጠበቅ ያለበት/ባት የቤት ስራ ምን ያህል ነው?
- ☐ ትምህርት ቤታችሁ የሙያ ስልጠና ፕሮግራሞችን ያቀርባል (ለምሳሌ፣ የእንጨት ሥራ፣ ግንበኝነት፣ የኤሌክትሪክ ሥራ፣ የጸጉር ማስተካከያ ሥራ፣ የቁንጅና ሥራ)? ለእነዚያ ፕሮግራሞች እንዴት ብቁ ይሆናሉ? እነዚህ ፕሮግራሞች ወይም የትምህርት ዓይነቶች የልምምድ ስራ ላይ ይቆጠራሉ?

የትምህርት ቤት አሰራሮችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ በትምህርት ሥርዓታችሁ ውስጥ ምን ዓይነት ቴክኖሎጂ ትጠቀማላችሁ እና ልጄ እንዴት ይጠቀመዋል/ትጠቀመዋለች?
- ☐ በትምህርት ቤታችሁ የአማካይ የክፍል መጠን ስንት ነው? በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ስንት አዋቂዎች እና ህጻናት አሉ?
- ☐ ትምህርት ቤታችሁ በትምህርት ዓመቱ የመስክ ጉዞዎችን ወይም ተመሳሳይ እድሎችን ያቀርባል?
- ☐ እንደ ትምህርት ሥርዓታችሁ አካል የጂም ክፍለ-ጊዜ ወይም እረፍት ጊዜ ትሰጣላችሁ? ተማሪዎች የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ የመጫወቻ ቦታ ወይም የቤት ውጪ ቦታ አላችሁ?
- ☐ ትምህርት ቤታችሁ የሙሉ-ጊዜ የነርስ ባለሙያ እና አማካሪ ሰራተኛ አለው?

የወላጅ ተሳትፎን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ ትምህርት ቤታችሁ የተቀናጀ የወላጅ መምህር ቅንጅት (ፓረንት ቲቸር አርጋናይዜሽን) (PTO) ወይም ተመሳሳይ ቡድን አለው? ከሆነ፣ ስራ ላይ አለው?
- ☐ ወላጆችን በክፍል ደረጃ እንዴት ያሳትፋሉ? በትምህርት ቤት ደረጃ?
- ☐ እንደ ጉልበተኝነት እና ጥቃት መከላከል ያሉ ጉዳዮች ላይ የትምህርት ቤት ኮሚቴ ወይም ሌሎች የወላጅ ተሳትፎ መንገዶች አሉ?

ጥያቄዎች ኢንግሊዝኛ ተማሪ ለሆኑ ቤተሰቦች

- ☐ ኢንግሊዝኛ የልጄ የቤት ቋንቋ አይደለም። ልጄ በትምህርት ቤታችሁ እንዲሻሻል/እንድትሻሻል እና እንዲሳከለት/ላት ለመርዳት ምን ዓይነት ድጋፎች ተቀምጠዋል?
- ☐ ትምህርት ቤታችሁ ኢንግሊዝኛ-ተናጋሪ ካልሆኑ ቤተሰቦች ጋር እንዴት ይግባባል እናም መረጃን እንዴት ያጋራል?
- ☐ አስተርጓሚን ወይም ሰነድ ወደ ቋንቋዬ እንዲተረጎም እንዴት መጠየቅ እችላለሁ?

ጥያቄዎች አካል ጉዳተኛ የሆነ/ች ልጅ ላላቸው ቤተሰቦች

- ☐ ልጄ የእድገት መዘግየት እንዳለው/ላት ከጠረጠርኩኝ፣ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጋቸው ለመወሰን የትምህርት ቤቱ ሂደት ምንድን ነው?
- ☐ ልጄ ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ(IEP) ወይም የ504 እቅድ አለው/ላት። አሁን ካሉበት ትምህርት ቤት ወደ ትምህርት ቤታችሁ የሚያደርጉትን ሽግግር ለመቆጣጠር ከእኔ እና ከልጄ ጋር እንዴት ትሰራላችሁ? እንደ ልጄ ተመሳሳይ አካል ጉዳተኝነት ያላቸው ተማሪዎችን ትምህርት ቤታችሁ እንዴት ይደግፋል?
- ☐ የትምህርት ቤት የመስክ ጉዞ ላይ አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ልጆች የሰራተኛ ቻፕሮን አሉ?
- ☐ ልዩ ፍላጎቶች ላላቸው ልጆች ራሱን-የቻለ ክፍል አላችሁ ወይስ አካታች ትምህርት ክፍሎችን ታቀርባላችሁ?
- ☐ በሰራተኞች ውስጥ ሙሉ-ጊዜ ቴራፒስት አላችሁ (የስራ፣ የንግግር፣ አካላዊ)?
- ☐ የIEP ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? በምስክር ወረቀቱ ፕሮግራም ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ምን መርሃ-ግብር እና ትምህርቶችን ትሰጣላችሁ?